ማውጫ

ክፍል 1 1
መግቢያ 1
የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ አመሰራረት፣ 1
የባለአደራ ቦርዱ ዓላማ 1
የባለአደራ ቦርዱ ሥልጣንና ተግባሮች:- 2
የባለአደራ ቦርዱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሃይል 2
ድርጅታዊ መዋቅር 2
የሰው ኃይል 3
የባለአደራ ቦርዱ የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description) 4
የባለአደራ ቦርዱ የፋይናንስ ምንጭ 5
የኦዲቱ ዓላማ 6
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 6
የክዋኔ ኦዲቱ የኦዲት አካባቢ 7
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 7
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 8
ክፍል ሁለት 9
የኦዲት ግኝቶች 9
ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን ንብረቶች አያያዝ፣ የዋጋ ግመታ እና አወጋገድ በተመለከተ ፣ 9
የባለአደራ ቦርድ ስራ አመራር ቦርድ እና የዋና ዳይሬክተር ኃላፊነት በተመለከተ፣ 9
የባለአደራ ቦርድ የክፍያ እና የንብረት አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣ 10
የባለአደራ ቦርድ እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣ 11
የባለአደራ ቦርድ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረት እና ሰነድ ርክክብን በተመለከተ፣ 12
የባለአደራ ቦርድ የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ 14
የባለአደራ ቦርድ የንብረት አገማመት፣ የመነሻ ዋጋ አወሳሰን ፣ የጨረታ ሂደት እና የተሸጡ ንብረቶች አረካከብን በተመለከተ፣ 16
የባለአደራ ቦርድ የስራ እና ሰራተኞች መመሪያን በተመለከተ፣ 17
የባለአደራ ቦርድ የክፍያና የወጪ አጠቃቀም መመሪያን በተመለከተ፣ 18
ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መሰብሰባቸውን፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 20
የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፣ 20
የፈረሱ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የተዘጋጀ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውኑን በተመለከተ፣ 21
የፈረሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብና የኦዲት ስራ በተመለከተ 22
ክፍል ሦስት 24
መደምደሚያ 24
ክፍል አራት 27
የማሻሻያ ሃሳብ 27
ቦርዱ በኪሳራ ከተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተቀየሩ የተላለፉለት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች ስር የተገለጹትን ግኝቶች በተመለከተ፤ 28
አባሪ 1 29
አባሪ 2 33
አባሪ 3 34

ክፍል 1

መግቢያ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ አመሰራረት፣

1. በአገራችን የነበረውን የዕዝ ኢኮኖሚ ስርዓት ወደ ነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት ለማሸጋገር በወጣው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ይዞታ የማዛወር ሂደት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለቤትነት ሲቀየር በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥያቄና ግዴታዎችን ተከታትሎ ለማስፈፀምና ሊከሰት በሚችለው የአፈፃፀም ክፍተት ላይ ጥንቃቄ ለማድረግ አንድ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ማቋቋም በማስፈለጉ የካቲት 5 ቀን 1988 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 17/88 "ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ" በሚል ስያሜ ተቋቋመ፡፡
2. የፕራይቬታይዜሽን እንቅስቃሴው በሽያጭ ብቻ ሳይሆን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የመዝጋት፣ ለቀድሞ ባለሃብቶች የመመለስ፣ በአክሲዮን ማህበርነት የማደራጀት ስራዎችን ሲጨምር ለቦርዱ ተጨማሪ ኃላፊነቶችን በመስጠት እንደገና በአዲስ መልክ "የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ " በሚል ስያሜ ሰኔ 20 ቀን 1992 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 208/92 ተሻሽሎ ተቋቋመ፡፡ ባለአደራ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ዓላማ፣ሥልጣንና ተግባር

የባለአደራ ቦርዱ ዓላማ

3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ዓላማው የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ በሚዛወሩበት፣ ወደአክሲዮን ማህበርነት በሚለወጡበት ወይንም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚመለሱበት ጊዜ ወደ አዲሱ የግል ባለቤት፣ ወደ አክሲዮን ማህበሩ ወይንም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መሰብሰብ፣ ዕዳዎችን መረከብና መክፈል፣ ንብረቶችን መረከብ፣ ማስወገድ እና ከነዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተልና ማስፈፀም እንዲሁም የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ማጣራት ነው፡፡

የባለአደራ ቦርዱ ሥልጣንና ተግባሮች:-

4. ባለአደራ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች አሉት፡-
    - የማይተላለፉ የልማት ድርጅት ተሰብሳቢ ሂሳቦች እና ዕዳዎችን የሚመለከቱ ሰነዶችን በመረከብ፣
        - ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦችን ከሚመለከታቸው ሶስተኛ ወገኖች ጋር ያስታርቃል፣
        - ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ይሰበስባል፣ለመሰብሰብ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣
        - ዕዳዎችን ለመንግስት እያቀረበ እንዲከፈሉ ያደርጋል፣
        - ሊሰበሰቡና ሊከፈሉ የማይችሉ ሂሳቦችን እያጣራ ከመዝገብ እንዲሰረዙ ለመንግስት ሃሳብ ያቀርባል፣
    - በፍርድ ቤት የተወሰኑ ወይንም በመንግስት መመሪያ ተለይተው ውክልና የተሰጣቸውን ዕዳዎች በቀጥታ ይከፍላል፡፡

የባለአደራ ቦርዱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

5. የባለአደራ ቦርዱ የሚመራው በማኔጅመንት ቦርድ ሲሆን የቦርዱ ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በቦርድ በተመረጠ አንድ ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም ለዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ 8 ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ የሊኩዴሽን ቨርቹዋል ቲም የስራ ሂደት አሉት፡፡ እነሱም በወሳኝ የስራ ሂደት ስር የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የድርጅቶች ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የድርጅቶች ሰነድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የሕግ ጉዳዩች ዳይሬክቶሬት፤ የሊኩዴሽን ቨርቹል ቲም የስራ ሂደት፤ በደጋፊ የስራ ሂደት ውስጥ የሰው ሀብት ልማት እና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ የሕዝብ ግንኙነት እና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት እና የለውጥ ትግበራ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡

የሰው ኃይል

6. ባለአደራ ቦርዱ በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ 72 ቋሚ ሰራተኞች እና 20 ኮንትራት ሠራተኞች በጠቅላላው 92 ሰራተኞቸ ያሉት ሲሆን ከቋሚ ሠራተኞች ውስጥ 38 ወንዶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 34 ደግሞ ሴቶች እንዲሁም ከኮንትራት ሰራተኞች ውስጥ 13 ወንዶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 7 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡የትምህርት ደረጃ ስብጥራቸውም ፣

ተ.ቁ	የትምህርት ደረጃ	ሴት	ወንድ	ድምር	በመቶኛ
1	በመጀመሪያ ዲግሪ	5	10	15	16.3%
2	ዲፕሎማ	25	16	41	44.6%
3	ከ7-12 ክፍል ያጠናቀቁ	6	6	12	13.0%
4	ከ1-6 ክፍል ያጠናቀቁ	2	7	9	9.8%
5	የትምህርት ደረጃቸው ያልተገለፀ	3	12	15	16.3%
	ድምር	41	51	92	100%

7. የባለአደራ ቦርዱ የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description)



የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ በሚዛወሩ፣ ወደአክሲዮን ማህበርነት በሚለወጡ ወይንም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚመለሱበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት፣ ወደ አክሲዮን ማህበሩ ወይንም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ተሰብሳቢ፣ተከፋይ ሂሳቦችንና ንብረቶችን የመረከብ ጥያቄ መቀበል፣ የርክክብ ዕቅድና መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ የሰነድና ንብረት ርክክብ መፈፀም፣ሰነድና ንብረት ማጓጓዝና ማደራጀት በመቀጠል በአምስት የስራ ሂደቶች ይከፋፈላል፡፡

- በፋይናንስ አስተዳደር ስር የሂሳብ መዝጋት፣ማስመርመር፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን ማጣራት ፣
- የሕግ ጉዳዮች መከታተል፣ ማስፈፀም ፣ ምክርና አስተያየት መስጠት፣
- የንብረት አስተዳደር ስራ እና የሰነድ አስተዳደር ስራ ውስጥ ጠቃሚና የማይጠቅሙትን መለየት፣ በሽያጭ የሚወገዱ ንብረቶችና ሰነዶች ዋጋ መገመት እና በጨረታ መሸጥ፣ የሚተላለፉና የሚወገዱ ንብረቶችና ሰነዶችን ማስተላለፍና ማስወገድ፤
- የሰራተኛ ጉዳዮች በተመለከተ ከስራ ውል የሚመነጭ የክፍያና የመረጃ ጥያቄን እና የጡረታ ጉዳዮችን ማስተናገድ ፣
- ገንዘብ መሰብሰብና መክፈል፣የማጠቃለያ ሂሳብ ማዘጋጀት፣ የድርጅት መክሰም ስራዎችን ማጠናቀቅና ግምገማ ማካሄድ፣ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው ማሰራጨት፣ ቀሪ ሀብትና ዕዳ ማስረከብ በመጨረሻም የተጠቃለለ የልማት ድርጅቶች ሀብትና ዕዳ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ ናቸው፡፡

የባለአደራ ቦርዱ የፋይናንስ ምንጭ

8. የባለአደራ ቦርዱ ስራውን የሚያካሂደው ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በተጨማሪም ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው ከተለወጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከሚተላለፍለት ንብረት እና ተሰብሳቢ ገቢ ሰብስቦ የሚያጠራቅምበትና በተመሳሳይ መልኩ ለድርጅቶቹ ግዴታዎች ወጪ የሚከፍልበት የልዩ ፈንድ ሂሳብ ከፍቶ እንዲያንቀሳቅስ በአዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

9. በዚህም መሰረት በ2001፣ 2002 እና በ2003 በጀት አመታት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ከመንግስት በጀት ብር 3,079,991.56፣ 3,007,106.66 እና 3,555,500.00 የተመደበለት ሲሆን ወደ ልዩ ፈንዱ ገቢ የሆነው ብር 27,880,737.62፣ ብር 39,688,184.54 እና ብር 49,040,961.19 ነው፤ በነዚህ በጀት አመታት ከተመደበለት በጀት ብር 3,065,441.56፣ ብር 2,961,275.95 እና ብር 3,354,808.93 እንዲሁም ከልዩ ፈንዱ ብር 46,800,178.29፣ብር 11,556,938.91 እና 42,254,062.77 ወጪ አድርጓል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

10. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፣ በባለአደራ ቦርዱ ውስጥ የሚከናወኑ ስራዎች ማለትም የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ በሚዛወርበት፣ ወደአክሲዮን ማህበርነት በሚለወጥበት ወይንም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት፣ ወደ አክሲዮን ማህበሩ ወይንም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በአግባቡ በመሰብሰብ ወደ ልዩ ፈንዱ ገቢ መሆናቸውን፤ ዕዳዎችን መረከብ እና ለተፈቀደላቸው ተከፋይ ሂሳቦች ብቻ ወጭ አድርጎ መክፈሉን ፤ የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶችን በአግባቡና በወቅቱ ሂሳብ ማጣራቱን እንዲሁም የተረከባቸው ንብረቶች አያያዝ፣አጠባበቅ እና አወጋገድ በመንግስት መመሪያ መሰረት መሆኑን እንዲሁም የዋጋ ግመታው (valuation) ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ ሲሆን አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ደግሞ አጥጋቢ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብና ባለአደራ ቦርዱ ያለበትን ተጠያቂነት ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

11. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2001 በጀት ዓመት እስከ 2003 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነው፡፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን የተለያዩ መረጃዎች በመመርመር፣ለሚመለከታቸው የባለአደራ ቦርድ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በተመረጡ ድርጅቶች በአካል

በመገኘት የኦዲት ማስረጃ በመሰብሰብ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች እና የክዋኔ ኦዲትን በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የኦዲት አካባቢ

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ይዞታቸው ከተቀየሩ ድርጅቶች እና ከፈረሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ሀብትና ዕዳ ተረክቦ የማጣራት ሂደት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

13. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡

እነሱም ፡-

I. ባለአደራ ቦርድ ወደ ግል ይዞታ ከተዛወሩ፣ ወደአክሲዮን ማህበርነት ከ ተለወጡ፣ ለቀድሞ ባለቤት ከተመለሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ኢኮኖሚያዊ ዋጋቸውን ሳያጡ ተሰብስበው ወደ ልዩ ፈንዱ ገቢ መደረጋቸውን ፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው ለሚገባቸው አካላት ብቻ የሚከፈሉ መሆናቸውን እንዲሁም በኪሳራ ምክንያት የተዘጉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ለማጣራት የሚያስችል የአሰራር፣ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት የተዘረጋ እና የተተገበረ መሆኑን ማጣራት ፣

II. ባለአደራ ቦርድ ይዞታቸው ከተቀየሩ ወይንም በኪሣራ ምክንያት ከፈረሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በደንብና መመሪያ መሰረት መሆኑን እንዲሁም የዋጋ ግመታው ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ስኬታማና ቅልጥፍናን በጠበቀ መልኩ መተግበሩን ማረጋገጥ ሲሆን፣

በተራ ቁጥር II ለተቀመጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ሁለት ንዑስ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል ፣

2.1 ባለአደራ ቦርዱ በኪሳራ ምክንያት የተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው የተቀየሩ የልማት ድርጅቶች ንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እያከናወነ መሆኑን ማጣራት፣

2.2 ባለአደራ ቦርዱ በኪሳራ ምክንያት ከተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተቀየሩ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን ንብረቶች የማስወገድ ሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣

ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

14. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issues) 38 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ለባለአደራ ቦርዱ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን ንብረቶች አያያዝ፣ የዋጋ ግመታ እና አወጋገድ በተመለከተ ፣

የባለአደራ ቦርድ ስራ አመራር ቦርድ እና የዋና ዳይሬክተር ኃላፊነት በተመለከተ፣

15. ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው የተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በአዋጁ መሰረት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

16. ባለአደራ ቦርዱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ ያሉ ስራዎች (ከልዩ ፈንዱ የሚፈፀም ማንኛውም ክፍያ) በስራ አመራር ቦርዱ የሚያፀድቅ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ስራዎች እንደ ጨረታ መነሻ ዋጋ መወሰን፣ የጨረታ ኮሚቴው በሚያቀርባቸው አማራጮች መሰረት ሽያጮች በሙሉ የማፅደቅ ስራዎች በማን እንደሚፀድቁ እና በምን መልኩ እንደሚከናወኑ በዋና ዳይሬክተርና በስራ አመራር ቦርድ በመለየት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያልተዘጋጀ እና ሁሉም ሥራዎች ለውሳኔ ወደ ስራ አመራር ቦርድ የሚሄዱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

17. ይህን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ አባል ተጠይቀው በቦርዱ ስራ አመራር (ማኔጅመንት) የሚቀርቡ ስራዎችን እንደሚያዩ ነገር ግን ሁሉንም ለስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ እንዲወሰን መመሪያ እንዳላስተላለፉ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የንብረት ሽያጭ ገቢውም ሆነ ከዚህ ጋር የሚገናኙ ወጪዎች ሁሉ ከልዩ ፈንድ ጋር ስለሚያያዙ ሁሉም የንብረት ሽያጭ በስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ አቋም ተወስዶ እየተሰራበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የስራ አመራር ቦርድ የሚሰበሰበው በወር አንድ ጊዜ በመሆኑ ውሳኔዎች በሙሉ አንድ ወር ስለሚጠብቁ አላስፈላጊ የስራ መዘግየት

ሊያስከትል እንደሚችል፣ እንዲሁም የሁሉም ስራዎች ውሳኔ የሥራው ክብደትና ቅለት ሳይገናዘብ በሥራ አመራር ቦርድ የሚወሰን በመሆኑ ማኔጅመንቱን ከተጠያቂነት የሚያገል፣ ተጠያቂነትን በሙሉ ወደሥራ አመራር ቦርዱ መተላለፉን የሚያሳይ መሆኑ ታምኗል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣

19. በባለአደራ ቦርድ የንብረት አያያዝ እና አወጋገድ መመሪያ ሊኖረውና በመመሪያው መሰረት ሊተገብር ይገባል፡፡

20. ባለአደራ ቦርድ ከሚገለገልበት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተሟላ ሁኔታ የማይተገብራቸው አንቀጾች መኖራቸው ታውቋል፡፡ (በአባሪ 2 ተያይዟል)

21. ወደ ባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች ሥራ አመራር ቦርድ ሳይፈቅድና ዋጋቸው ሳይከለስ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም እየተከራዩ መገኘታቸው፣ በናሙና ከታዩት 13 የተለያዩ መጋዘኖች፣ ሱቆችና ቢሮዎች ውስጥ 12ቱ (92%) በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ዋጋቸው ያልተከለሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውስጥ ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ንብረቱን ሳይረከቡ ብር 4,394.32፣ ደብረብርሃን ብርድ ልብስ ፋብሪካ ብር 223,129.98 እና አዲስ ጎማ ፋብሪካ ብር 1,327,635.24 የሚያወጡ ንብረቶች ለፋብሪካዎቹ ከመመሪያው ውጭ ያለጨረታ በመዝገብ ዋጋ መሸጣቸው እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጪ ድርጅት ንብረት የሆነ አንድ ሞተር ሳይክል ቀደም ሲል በጨረታ የተሸጡ ሞተር ሳይክሎችን እንደመነሻ ዋጋ በመውሰድ ያለጨረታ የተሸጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

23. ይህን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ አባል ተጠይቀው የመንግስት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 9/2003 ችግር እንዳለበት ተገልፆ በዋና ዳይሬክተር በኩል ያልቀረበላቸው መሆኑን፣የአዲስ ጎማ ፋብሪካ በተመለከተ መለዋወጫው ለፋብሪካው ብቻ የመጣ በመሆኑ ሌላ ፈላጊ አካልም ስለሌለው ለፋብሪካው እንዲሸጥ መወሰኑን፣ የንብረቶችን ኪራይ በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የተላለፉት ንብረቶች ካርታና ፕላን

እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት እየተከራዩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው አዲስ ጎማ መለዋወጫ ንብረቶች ለሌላ አካል በጨረታ እየተሸጡ ስለሚገኙ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ባለአደራ ቦርዱ የድሬደዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ንብረትን ባልተረከበበት ሁኔታ ከመንግስት የንብረት መመሪያ ውጪ ንብረቶችን ያለጨረታ መሸጥ መመሪያን ያልተከተለ ከመሆኑ ባሻገር መንግስት ሊያገኘው የሚገባውን ኢኪኖሚያዊ ጥቅም የሚያስቀር መሆኑ ታምኖበታል፡፡

የባለአደራ ቦርድ እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣

25.ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ወይም የጋራ መግባቢያ ሰነድ (መመሪያ) ሊኖር ይገባል፡፡

26.በኦዲቱ ወቅት ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና ባለአደራ ቦርድ በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ባለአደራ ቦርዱ ያልተዘጋ ሂሳብ የሚረከብ መሆኑ (አደይ አበባ ድርና ማግ ፋብሪካ የ8 ዓመት ሂሳብ ሳይዘጋ)፣ ሰነዶች የሚጠፉ መሆኑ (በርክክብ ላይ የሚገኘው የቀድሞው ውሃ ጉድጓድ ስራዎች ድርጅት የጥቃቅን ወጪዎች መክፈያ ቫውቸር በቁጥር 30፣ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቫውቸር በቁጥር 13 እና የቼክ መክፈያ ቫውቸር በቁጥር 12 ባጠቃላይ 55 ቅጠሎች በርክክብ ወቅት አለመገኘታቸው) እና በርክክቡ ወቅት ያልተገኙ ሰነዶችን በተመለከተ ተጠያቂ የተደረገ አካል አለመኖሩ ታውቋል፡፡

27.በናሙና ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ ብሄራዊ አስጎብኝ ድርጅት፣ የጮራ ጋዝና ኬሚካል ውጤቶች ድርጅት ከውሉ ውጪ ለሰራተኞች ጥቅማጥቅም እንዲከፍሉ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ባለአደራ ቦርድን ያዘዘ መሆኑ፣ ኪራይን በተመለከተ ፋፋ ምግብ አክሲዮን ማህበር ከተሸጠ በኋላ ለገዥው ያልተላለፉ ንብረቶችን ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የኪራይ ውል በ2002 ዓ.ም ከተዋዋለ በኋላ አለአግባብ ባለአደራ ቦርዱን የኪራይ ገንዘብ እንዲሰበስብ ያደረገ እና ወደቦርዱ

መተላለፍ የማይገባው ካቶ ክሬን ባለአደራ እንዲረከብ በማድረግ ለአሰላ ብቅል ፋብሪካ በጨረታ መነሻ ዋጋ እንዲሸጥ ያዘዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

28. ይህን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ አባል ተጠይቀው መደበኛ ምክክር ጊዜ የሌላቸው መሆኑን፣ ሆኖም ችግሮች ሲያጋጥሙ በመመካከር ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣ የአደይ አበባ ድርና ማግ ፋብሪካ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር የመጣ ሲሆን ሰነዶች ስለመጥፋታቸው በባለአደራ ቦርድ በኩል የተገለፀላቸው ነገር አለመኖሩን፤እንዲሁም ማከራየትን በተመለከተ የፋፋ ምግብ አክሲዮን ማህበር ንብረቶችን በሽያጭ እስኪያስወግዱ ድረስ ውል ተዋውለው ኪራይ እንዲሰበስቡ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

29. ከላይ እንደተገለፀው ያልተዘጋ ሂሳብ ወደባለአደራ ቦርድ በመተላለፉ በቦርዱ ላይ የስራ ጫና መፍጠሩ፣ በርክክብ ወቅት የጎደሉ ሰነዶች ምን ይዘው እንደጠፉ ለማወቅ አስቸጋሪ መሆኑ እና በኃላፊነት የሚጠየቅ አካል አለመኖሩ፣የሰራተኞች ክፍያን በተመለከተ ከፕራይቬታይዜሽን ጋር ባለመናበባቸው ምክንያት በባለጉዳዮች ላይ መጉላላትን የፈጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡

የባለአደራ ቦርድ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረት እና ሰነድ ርክክብን በተመለከተ፣

30. ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረቶችን ሲረከብ በመጠን፣ በአይነት እና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው ሊረከብ ይገባል፡፡

31. ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለባለአደራ ቦርድ ንብረቶችን እንዲረከቡ ካሳወቃቸው ድርጅቶች በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ አዲስ ጎማ ፋብሪካ፣ ደብረብርሃን ብርድልብስ ፋብሪካ እና የአዲስ የመለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር የእያንዳንዱ ንብረት ዓይነትና የዋጋ ዝርዝር አለመላኩ እና በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጅ በ(restructuring) ጥናቱ መሰረት ከካፒታል

ውጭ የሆነ ብር 57,053,479 የሚያወጣ ንብረት በጥቅል ወደ ባለአደራ ቦርድ እንዲተላለፍ መደረጉ እንዲሁም ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ 18 ሺህ ላይን አይተም እና ከብር 24 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ንብረት ያለርክክብ ሠነድ ለቦርዱ መተላለፉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስዕል 1.በአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር መጋዘን ውስጥ ባልተደራጀ ሁኔታ በጥቅል የተላለፉ ንብረቶች በከፊል

32. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የንብረቶች ዝርዝር ባለመታወቁ ባለአደራ ቦርዱ በአካል የተገኙትን ንብረቶች ብቻ እንዲረከቡ በመደረጉ ወደገዥው (ወደአዲሱ ባለቤት) ያልተላለፉትን ንብረቶች በሙሉ መረከቡን ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ እንዲሁም በድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሰራተኞች ንብረቶቹን ሳይረከቡ ቁልፍ ይዘው ሲያንቀሳቅሱ የቆዩ መሆኑ፣ ህጋዊ የንብረት ርክክብ ሳይካሄድ ሠራተኞቹ በኮንትራት ተቀጥረው ስራው እንዲቀጥል የተደረገ መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ይህም አሰራር ንብረቶች በጥንቃቄና በኃላፊነት ያልተያዙ መሆኑን ያሳያል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ

33. ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች በኃላፊነት ሊይዝና ሊጠብቅ እንዲሁም መቆጣጠሪያ መዛግብት ሊያዘጋጅ፣ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግ እና በውክልና ሽያጪ እንዲወገዱ የተሰጡ ንብረቶች አፈጻጸም ሊከታተል ይገባል፡፡

34. ባለአደራ ቦርድ የተረከባቸውን ንብረቶች መቆጣጠሪያ መዛግብት የመያዝ፣ ንብረቶችን የመረከብና ወጪ የማድረግ ሥራን አንድ ሰው እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጪ ውል የተፈራረመ ቢሆንም ከ1997 ዓ.ም እስከ 2003 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትል ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡(የአክሲዮን ማህበራት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል)

35. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ባለአደራ ቦርዱ ከተረከባቸው የተለያዩ ንብረቶች ውስጥ በአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን የድርጅቶቹ ንብረቶች እና ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸው ንብረቶች በአንድ መጋዘን ውስጥ ንብረቶቹን በከፊል በቦታ በመለየት ጥበቃው በሌላ አካል ስር ሆኖ ከላይ ክፍት በሆነ ቦታ መቀመጣቸውን እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶቹን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ንብረቶች ለመኖራቸው (Existance) የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ የማያውቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የባለአደራ ቦርድ ንብረቶች *የአክሲዮን ማህበሩ ንብረቶች*

ስዕል 2. *በአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር መጋዘን ውስጥ በቦታ ተለይተው የንብረቱን ደህንነት በማያስጠብቅ ከላይ ክፍት በሆነ ክፍልፋይ የተቀመጡ የባለአደራ ቦርዱ ንብረቶች በከፊል*

36. ይህን በተመለከተ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ንብረቶቹን ተረክበው የሚያስቀምጡበት የተዘጋጀ መጋዘን (ማቆያ) ቦታ ባለመኖሩ ከድርጅቶቹ ጋር በመነጋገርና በመከራየት ንብረቶቹን ያስቀመጡ መሆኑን እንዲሁም የንብረቶቹን አያያዝ ለማሻሻል በተዘረጋው አዲስ የቁጥጥር ስርዓት መሰረት የንብረቶች መቆጣጠሪያ መዝገብ ንብረቶችን ከተረከቡት ሰራተኞች እጅ ወደ ዋናው መ/ቤት እየተሰበሰቡ መሆኑ፣ ንብረቶቹን የምንረከበው ለማስወገድ ስለሆነ ቆጠራ የማይደረግ መሆኑን፣ በአክሲዮን ማህበራት በውክልና እንዲወገዱ የተቀመጡ ንብረቶችን ከ2003 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ የክትትል ስራውን በአካልና በደብዳቤ መጀመራቸውን ገልጸዋል ፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ንብረቶቹ ለደህንነታቸው አስተማማኝ ባልሆነ ቦታ መቀመጣቸው እንዲሁም ንብረቶቹን ለመቆጣጠር የሚደረግ የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት እንደ ቆጠራ የመሳሰሉት አለመካሄዳቸው ንብረቶቹ በአግባቡ መጠበቃቸውን እና በተሟላ ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ በየጊዜው የማይረጋገጥ መሆኑን ያሳያል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አገማመት፣ የመነሻ ዋጋ አወሳሰን ፣ የጨረታ ሂደት እና የተሸጡ ንብረቶች አረካከብን በተመለከተ፣

38. የንብረቶች ዋጋ በዝርዝሩ መሰረት በባለሙያ ሊገመት፣ በባለሙያ የማይገመቱ ንብረቶች ሆነው ሲገኙ በአካል በመገኘት ይዘቱን ማወቅ፣ ተመሳሳይ ዕቃ ከሚያቀርቡ አቅራቢዎች የወቅቱን የገበያ ዋጋ መረጃ መሰብሰብና የመነሻ ዋጋ መወሰን እንዲሁም ለጨረታ የሚወጡ ንብረቶች አይነትና መጠን በጨረታ ሰነድ ላይ ሊጠቀስ እና ንብረቶች በጨረታ ውጤቱ መሰረት ለገዥው ሊተላለፉ ይገባል፡፡

39. በኦዲት ከታዩት ድርድቶች ውስጥ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 35,145,548.17 የመነሻ ዋጋ ሲሰላ ባለው እዳ እና ወደፊት ስራዎችን ለማከናወን ሊወጡ የሚችሉ ወጪዎችን ታሳቢ በማድረግ የተሰጠ እንጂ የድርጅቱ ንብረት በባለሞያ ተጠንቶ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያልተሰጠ መሆኑ እና ጨረታ ሲወጣ የጨረታ ሰነድ ዝርዝር ላይ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እና ዋጋ ያልተሰጠበት መሆኑ፤

40. የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ለጨረታ የቀረቡ 13 የቡና ማበጠሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና መጋዘን የዋጋ ግመታ በባለሞያ አለመታየቱ፣ ጽ/ቤቶችና የቡና ማበጠሪያዎች በውስጣቸው የያዙት የማበጠሪያ ማሽን ፣የቋሚ ንብረት ብዛት እና አይነት ሳይገለፅ የመነሻ ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑ፣ የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) ሽያጭ ተፈፅሞ ለገዥው ርክክብ ሲደረግ ወደገዥው መተላለፍ ከነበረበት ንብረት ውስጥ 52 አይነት ቋሚ ንብረት ያልተላለፈ መሆኑ እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን በብር 555,000 ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ዋጋ የተሰጠው በስህተት ነው በማለት አሸናፊው ለዋስትና ባስያዘው ብር 55,000 ከመነሻ ዋጋ በ45% አንሶ የተሸጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

41. ይህን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፋብሪካውን ንብረቶች በዋስትና ይዞ ያበደረው ባንክ ንብረቶቹን የገመተው በመነሻ ዋጋ ከተገመተው በጣም ባነሰ በመሆኑና እዳን መነሻ በማድረግ መገመት የሊኩዴሽን ደንብ የሚፈቅድ መሆኑን፤ ማደያና ዲፖው

ጠቅላላ የድርጅቱ አካል ስለሆነ ለብቻው ባይጠቀስም በጥቅል እስከተሸጠ ድረስ አለመጠቀሱ ያስከተለው ችግር እንደሌለ እና የንብረት ርክክቡን በተመለከተ ገዥዎች የተጫረቱበትን ንብረት ተሳስበው መረከብ እንደሚችሉ ነገር ግን ገዥዎች ያልተረከብነው ንብረት አለ ብለው ያቀረቡት አቤቱታ አለመኖሩን፣ የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን በማስታወቂያ በተፈጠረ ስህተት መገኘት የማይችል ዋጋ የተሰጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ ሽያጩ በጨረታ ከተሰጠው ዋጋ ባነሰ እንዲፈፀም መወሰኑን ገልፀዋል፡፡

42.ኦዲት ተደራጊዎች ከላይ የተገለፀውን መልስ ቢሰጡም እዳን መነሻ ማድረግ ይቻላል የሚል የሊኩዴሽን ደንብ ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣ የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) የንብረት ርክክብ የጨረታ አሸናፊው ዝርዝሩን በማያቁበት ሁኔታ ተሳስበው መረከብ ነበረባቸው መባሉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

43.በአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር የጨረታ ሰነድ ውስጥ ሌሎች ንብረቶች በዝርዝር ተገልፀው ዋጋ የተሰጠባቸው ሲሆን ማደያና ዲፖው ግን በዝርዝር ውስጥ ተገልፆ ዋጋ ያልተሰጠበት በመሆኑ ዋጋ ቢሰጥበት ኖሮ የተሻለ ዋጋ ሊገኝ ይችል እንደነበር፣ የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) ለገዥው ያልተላለፉ ንብረቶች በቦርዱ ወይንም በግለሰቦች ቁጥጥር ሥር ስለመሆናቸው ማረጋገጥ የማይቻልና ተጠያቂነትን የማያጠናክር መሆኑን፣ የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን ጨረታን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ የቦርዱን ጥቅም ያስጠበቀ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የስራ እና ሰራተኞች መመሪያን በተመለከተ፣

44. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረታዊ ዓላማ በመከተል የባለአደራ ቦርድ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ ሊዘጋጅና በስራ አመራር ቦርድ ሊፀድቅ ይገባል፡፡

45. የባለአደራ ቦርዱ መቋቋሚያ አዋጅ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረታዊ ዓላማ በመከተል የባለአደራ ቦርድ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል ቢልም መመሪያውን ያላዘጋጀ መሆኑ ነገር ግን በሐምሌ 1/2003 ዓ.ም የሊኩዴሽን ቨርቹዋል ቲም ስራና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር የፀደቀ መሆኑ፣ በዚህም መመሪያ የተካተተው የሊኩዴሽን

ቡድን የአበል ክፍያ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስን መሰረታዊ አላማ ያልተከተለና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ለሊኩዴሽን ቡድን አስተባባሪ የነዳጅ ፍጆታ መጠን ያልተቀመጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

46. ይህን በተመለከተ አንድ የስራ አመራር ቦርድ አባል ተጠይቀው በሰጡት መልስ የፀደቀው የሊኩዴሽን ቨርቹዋል ቲም መመሪያን በተመለከተ ለቦርድ አለመቅረቡን፣ ለሊኩዴሽን ቡድን የተፈፀመው ክፍያ ከፈረሰው ድርጅት ከራሱ ወጪ የሚከፈልና የበጀት ጥያቄ የማያስከትል በመሆኑ የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መከተል እንዳላስፈለጋቸው ገልፀዋል፡፡

47. የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊዎች ይህን መልስ ቢሰጡም የፈረሰ የልማት ድርጅት ከፈረሰበት እለት ጀምሮ የመንግስትን የበጀት አሰራርን ተከትሎ የሊኩዴሽን ስራውን የሚያከናውን በመሆኑ በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ለሚተዳደሩ ሰራተኞች ከህጉ ውጭ ተጨማሪ አበል መክፈል ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

48. የሊኩዴሽን ሂሳብ የባለገንዘቦች (ክሬዲተርስ) እና የመንግስት ሃብት በመሆኑ ለስራው የሚያስፈልጉ ወጪዎች በመንግስት ህግና ደንብ መሰረት በጥንቃቄ ካልወጡ ባለገንዘቦች ገንዘባቸውን ሊያገኙ የማይችሉ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት ተቀጣሪ የሆኑ ሰራተኞች ከሚተዳደሩበት ህግና ደንብ ውጭ የበጀት ጥያቄ አያስነሳም በማለት ተጨማሪ ክፍያ መፍቀድ እና ተሽከርካሪ ከነነዳጁ ያለገደብ መስጠቱ በመ/ቤቱ ውስጥ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ሊያደርግና እና የውስጥ ቁጥጥር ስርአቱን ሊያላላ ይችላል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የክፍያና የወጪ አጠቃቀም መመሪያን በተመለከተ፣

49. ባለአደራ ቦርድ የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ክፍያዎችን ለማከናወን መመሪያ ሊያዘጋጅና የክፍያ እና የወጪ አጠቃቀም በስራ አመራር ቦርዱ እየታየ እና እየተፈቀደ ሊከፈል ይገባል፡፡

50. የሊኩዴሽን ወጪዎችን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ እንደማያየውና እንደማያፀድቀው፣ ለሊኩዴሽን ስራ ማስኬጃ እንዲወጣ በሊኩዴሽንና የድርጅቶች ንብረት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ መፈቀዱ፣ በተፈቀደው መሰረት ለጥቃቅን ወጪ በየወሩ እንዳለቀ የሚተካ ለቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ብር 3,000 እና ለአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 2,500 እየተከፈለ እና ከ2001-2003 በጀት ዓመት ለጥቃቅን ወጪዎች ተብሎ በድምሩ ብር 172,037.56 ወጪ መደረጉ፣ ክፍያውም በዋናነት ለመስተንግዶ፣ ለነዳጅና ለመሳሰሉት የሚውል መሆኑ፤

51. ባለአደራ ቦርዱ ከአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከተረከበው ነዳጅ እንዲጠቀም በስራ አመራር ቦርድ ሳይፈቀድ ተጠቅሞ መገኘቱ፣ በርክክብ ወቅት 7,410 ሊትር ቤንዚን እና 5,725 ሊትር ናፍጣ በህዳር 2001 ዓ.ም የተረከቡ ቢሆንም በካርድ ባላንስ መሰረት "oct 17/2011" 192 (2.59%) ሊትር ቤንዚን እና "May /2011" 1257 (22%) ሊትር ናፍጣ የቀረ እና 7,218 ሊትር ቤንዚን ና 4,468 ሊትር ናፍጣ የተጠቀሙበት መሆኑ ታውቋል፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በባለአደራ ቦርዱ መቋቋሚያ አዋጅ በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 3 የስራ አመራር ቦርዱ የባለአደራ ቦርዱን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ የማጣራት ሂደት ሕጋዊ ስርአቱን ተከትሎ መፈፀሙን ያረጋግጣል ይላል በዚህ መሰረት የሊኩዴሽን ወጪዎቹም የቦርዱ ሃላፊነት በመሆናቸው ወጪዎችን አለማየትና አለማፅደቅ ኃላፊነትን ካለመወጣቱም ባሻገር ወጪዎች በትክክለኛው መንገድ መውጣታቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ በአደራነት የተረከበውን ነዳጅ የበላይ ኃላፊዎች ሳይፈቅዱ መጠቀም የተቀዳው ነዳጅ በአግባቡ ስራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለመቆጣጠር የማያስችልና ለብክነት የሚያጋልጥ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መሰብሰባቸውን፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፣

53. ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ርክክብ እስከተፈጸመበት ዕለት ያለውን የሂሳብ መዝጋት ስራ እንዲከናወንና በውጪ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. ባለአደራ ቦርዱ ውስጥ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስራ ተረክቦ ለማከናወን በየበጀት ዓመቱ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ክንውኑ ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ዝርዝር	በጀት አመት		
		2001	2002	2003
1	ሂሳብ መዝጋት	50%	40%	47%
2	ሂሳብ ማስመርመር	42%	31%	25%
	አማካይ በመቶኛ	46%	35.5%	36%

ሰንጠረዥ1. የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዕቅድ ክንውን መጠን በመቶኛ

55. ይህን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሥራ ባህሪው ሰራተኞች ወደተለያየ ቦታ የሚያስኬድና በዕቅድ ከተያዘው ሥራ ይልቅ የክፍያ ጥያቄዎችና ባለጉዳዮችን በማስተናገድ ላይ ስለሚተኮር በእቅዱ መሰረት መስራት እንዳልተቻለ ገልፀዋል፡፡

ተ.ቁ	ሰራተኛ	በጀት ዓመት			
		2000	2001	2002	2003
1	ሥራ ላይ ያሉ ቋሚ ሰራተኞች በቁጥር	17	15	17	14
	በመቶኛ በመጨመር/በመቀነስ	-	12%	12%	18%

ሰንጠረዥ 2. የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር የሰው ኃይል ብዛት

56. የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊዎች ከላይ የተመለከተውን መልስ ቢሰጡም የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዕቅድ ክንውን ዳይሬክቶሬቱን ካለው የሰው ኃይል (ሰንጠረዥ 2) ጋር ሲነፃፀር በ2001 በጀት አመት የሰው ኃይል ቁጥር በ2 ወይም 12% ሲቀንስ የዕቅድ ክንውኑ 46% መሆኑ፣ በ2002 በጀት አመት የሰው ኃይል ቁጥር በ2 ወይንም 12% ሲጨምር የዕቅድ ክንውኑ 35.5% መሆኑ፣ በ2003 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ቁጥር በ3 ወይም 18% ሲቀንስ ዕቅድ ክንውኑ በ36% ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የስራ ክፍሉ የዕቅድ አፈጻጸሙ ከሰው ኃይል ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ የሌለው በመሆኑ የሰው ኃይል ዕጥረት የሚለው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡

57. ባለአደራ ቦርዱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች እንዳይታወቅና የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ (Consolidated Financial report) እንዳይዘጋጅ ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የፈረሱ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የተዘጋጀ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውኑን በተመለከተ፣

58. ባለአደራ ቦርድ በተለያየ ምክንያት የሚፈርሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ማጣራት ስራ ለመስራት ዕቅድ እና ድርጊት መርሃ ግብር ሊያዘጋጅ ይገባል፣

59.በናሙና ከታዩት በባለአደራ ቦርድ ሂሳብ ማጣራት ስራ ከተከናወነባቸው ድርጅቶች ውስጥ የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ስራውን ለመስራት በቅድሚያ የተዘጋጀ ዕቅድ እና የድርጊት መርሃ ግብር አለመኖሩ ፤

60. የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ከፈረሰ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ለ10 ዓመታት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ከ 2001 እስከ ህዳር 2004 ዓ.ም ለአራት ዓመታት የሂሳብ ማጣራት ስራ በባለአደራ ቦርድ እየተሰራ ቢሆንም ስራው ያልተጠናቀቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

61.በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ለስራው ዕቅድ አለማዘጋጀት ስራውን በተሻለ ጊዜና ወጪ ለመስራት እንዳይቻል ከማድረጉም በተጨማሪ የቡድኑን እና የመ/ቤቱን የሂሳብ ማጣራት (ሊኩዴሽን) ስራ አፈጻጸም ለመለካት የማያስችል አድርጎታል፡፡

የፈረሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብና የኦዲት ስራ በተመለከተ

62.በህግ ወይም በኪሳራ የሚፈርሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸው በወቅቱ ተዘግቶ እና ያላቸው ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ ሪፖርት ሊደረግና ሂሳቡ ሊመረመር ይገባል፡፡

63.በናሙና ከታዩት የሂሳብ ማጣራት ስራዎች የቡና ግዥና ሽያጪ ድርጅትና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የሚዘጋጅ ቢሆንም ሂሳቡ በውስጥም ሆነ በውጪ ኦዲተር ተመርምሮ እንደማያውቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

64.ይህን በተመለከተ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በሊኩዴሽን ህግ ስራውን አጠናቆ ለዋና ኦዲተር ሪፖርት ማቅረብ እንጂ በየዓመቱ ማስመርመር ኃላፊነት አይሰጥም ብለዋል፡፡

65.የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 44 ንኡስ አንቀፅ 1 "የሂሳብ አጣሪዎች ድርጅቱ ትርፍ ሃብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ ሃብትና

የእዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለዋና ኦዲተር ግልባጭ ያደርጋሉ ዋና ኦዲተርም የሚሰጠው አስተያየት ካለ ወዲያውኑ ይሰጣል” ይህም በመጨረሻ ሂደቱ ላይ ስለሚኖር አስተያየት እንጂ የአፈፃፀም ሂደቱ ኦዲት አይደረግ የሚል ባለመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

66. የሂሳብ ማጣራት (ሊኩዴሽን) ስራ በወቅቱ በውስጥ ኦዲተር ወይንም በዋናው ኦዲተር አፈፃፀሙና የሂሳብ አያያዙ ኦዲት ካልተካሄደ በአሰራሩ ላይ ያሉ ግድፈቶችን በወቅቱ ለይቶ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

67. ባለአደራ ቦርዱ የተቋቋመበትን ዋና ዓላማ ለማስፈጸም በተለያየ መንገድ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት ልማት ድርጅቶች የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መሰብሰብ፣ ዕዳዎችን መረከብና የሚፈርስ ልማት ድርጅትን ሂሳብ ማጣራት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በባለአደራ ቦርዱ ውስጥ የሚከናወኑ ይዞታቸው የተቀየሩ እና የፈረሱ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ሀብትና ዕዳ ተረክቦ የማጣራት ሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር በባለአደራ ቦርዱ ሀብትና ዕዳ ተረክቦ የማጣራት ሂደት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ነው ማለት አያስችልም፡፡

- የባለአደራ ቦርዱ ስራዎች በሙሉ ለውሳኔ ወደ ስራ አመራር ቦርድ የሚሄዱ በመሆናቸው የስራ መዘግየት የሚያስከትል መሆኑ፣
- የባለአደራ ቦርዱ የንብረት አያያዝ ደህንነታቸውን የማያረጋግጥ እና ንብረቶችን ከመመሪያ ውጭ ያለጨረታ የሚያስወግድ መሆኑ፣
- ወደባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች ከዓላማው ውጭ እየተከራዩ መገኘታቸው፣ የተከራዩትም ቢሆን ዋጋቸው በየወቅቱ የማይከለሱ መሆናቸው፣
- ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጋር በቅንጅት የሚሠራበት የጋራ መግባቢያ ሰነድ (መመሪያ) አለመዘጋጀቱ፣
- ባለአደራ ቦርድ ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረቶችን ሲረከብ በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው የማይረከብ መሆኑ፣
- ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ንብረቶች ለመኖራቸው(Existance) የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ የማያውቅ መሆኑ፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን ለማስወገድ ከአክሲዮን ማህበራት ጋር የውክልና ሽያጪ ውል የተፈራረመ ቢሆንም ከ1997 ዓ.ም እስከ 2003 በጀት ዓመት አጋማሽ ንብረቶች ያሉበት ሁኔታ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣
- የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ንብረት እና በቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት 13 የቡና ማበጠሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና መጋዘኖች በባለሞያ ተጠንቶ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ጨረታ ወጥቶ ሲሸጥ የጨረታ ሰነድ ዝርዝር ላይ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እና ዋጋ ያልተሰጠበት መሆኑ፣
- የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት የዲላ ጽ/ቤት ኤ ሽያጭ ተፈጽሞ ለገዥው ርክክብ ሲደረግ መተላለፍ የነበረበት 52 ቋሚ ንብረት ያልተላለፈ መሆኑ፤
- የባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ መሠረታዊ አላማ በመከተል ሰራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የሥራ አመራር ቦርድ ለሂሳብ ማጣራት ስራ የሚወጡ ወጪዎችን የማያጸድቁና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ መሆኑ፣
- የድርጅቶች ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዕቅድ ክንውን ዝቅተኛ መሆኑ፣ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ የማይታወቅና የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የፈረሱ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ማጣራት ስራን ለማከናወን በቅድሚያ ዕቅድ እና የድርጊት መርሃ ግብር ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የፈረሱ የልማት ድርጅቶች የሂሳበ ማጣራት ስራን አፈጻጸሙና ሂሳቡ በውስጥም ሆነ በውጪ ኦዲተር ተመርምሮ የማያውቅ መሆኑ፣

68. በአጠቃላይ ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የፈረሱ የልማት ድርጅቶች ሃብትና ዕዳ ተረክቦ የማጣራት ስራ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የመፈጸም ችግር ያለበት መሆኑን ለመረዳት ያስችላል፡፡ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳብ

69.ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን ንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ፣ የዋጋ ግመታ እና አወጋገድ ስር የተገለጹ ግኝቶችን በተመለከተ ፣

- ባለአደራ ቦርዱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ በስራ አመራር ቦርድ እና በዋና ዳይሬክተር የሚሰሩ ስራዎችን በመለየት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ወደባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች አስፈላጊው መረጃ ተሟልቶላቸው ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ባለአደራ ቦርዱ እየተጠቀመበት ያለው የንብረት አወጋገድ መመሪያ የማያሰራው መሆኑን አሳውቆ ለስራው ተስማሚ የሆነ መመሪያ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ስራ ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡
- ባለአደራ ቦርዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተለይ ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጋር (በሪፖርት አደራረግ፣ በዕቅድ አዘገጃጀት ወዘተ) በቅንጅት የሚሰራበትን የጋራ መግባቢያ ሰነድ (መመሪያ) አዘጋጅቶ ሊጠቀም ይገባል፡፡
- ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶችን በሚረከብበት ጊዜ በመጠን፣በዓይነትና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው ሊረከብ ይገባል፡፡
- በቀላሉ ሊንቀሳቀሱ እና ሊጠፉ የሚችሉ፣ውድ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች የመሳሰሉትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ዕቃዎቹ ለመኖራቸው(Existance) የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ከአክሲዮን ማህበራት ጋር የውክልና ሽያጪ ውል የተገባባቸው ንብረቶች ሽያጪ እና ንብረቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል አመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ባለአደራ ቦርዱ በሽያጭ የሚያስወግዳቸው ቋሚ ንብረቶች የመነሻ ዋጋ ግመታ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተሰርቶ ለጨረታ ሊቀርቡ፣ጨረታ የወጣባቸው ንብረቶች ዓይነትና መጠን በጨረታ ሰነድ ላይ ሊጠቀስ እና ንብረቶች በጨረታ ውጤቱ መሰረት ለገዥው በትክክል መተላለፋቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ቦርዱ በኪሳራ ከተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተቀየሩ የተላለፉለት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች ስር የተገለጹትን ግኝቶች በተመለከተ፤

- ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ መሰረታዊ አላማ በመከተል በመ/ቤቱ ወጥ የሆነ የሰራተኞች መመሪያ አዘጋጅቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

- የስራ አመራር ቦርዱ የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የሚወጡ ወጪዎች ህጋዊ ስርአቱን ተከትሎ መፈጸሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ ማጣራት ስራዎች ከመጀመራቸው በፊት ዕቅድ እና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ሊተገበር ይገባል፡፡

- የፈረሱ የልማት ድርጅቶች የሂሳበ ማጣራት ስራን አፈጻጸሙና ሂሳቡ በውስጥ ወይንም በዋና ኦዲተር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issue)	የኦዲት መስፈርት (Audit Criteria)
1.የባለአደራ ቦርድ ወደ ግል ይዞታ ከተዛወሩ፣ ወደ አክሲዮን ማህበርነት ከተለወጡ፣ ለቀድሞ ባለቤት ከተመለሱ ወይንም በኪሳራ ምክንያት ከተዘጉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ኢኮኖሚያዊ ዋጋቸውን ሳያጡ ተሰብስበው ወደ ልዩ ፈንድ ገቢ መደረጋቸውን እንዲሁም ተከፋይ ሂሣቦች በአግባቡ ተጣርተው ለተፈቀደላቸው አላማ ብቻ ወጪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር፣ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት የተዘረጋ እና የተተገበረ መሆኑን ማጣራት፣	1. ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ ምክንያት ይዞታቸው የሚቀየሩ እና በአዋጅ እንዲፈርሱ ከተወሰነ ጊዜ ጀምሮ ራሳቸውን ለፕራይቬታይዜሽን ሲያዘጋጁ፤ተሰብሳቢ፣ተከፋይ እና ንብረትን በተመለከተ በምን አይነት ሁኔታ መዘጋጀትና ርክክብ መፈጸም እንዳለበት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል።
1.1.ቦርዱ በኪሳራ ከሚዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተቀየሩ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ተሰብስበው ወደ ልዩ ፈንድ ሂሳብ ገቢ መሆናቸውን፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው ለተፈቀደ ክፍያ ብቻ የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ አሠራር ስርአት መዘርጋቱን ማጣራት፣	2. ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ባለአደራ ቦርድ ንብረቶችን ሲረከብ በመጠን፣ በአይነትና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው ሊረከብ ይገባል።
	3. ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር ቅንጅታዊ (በሪፖርት፣ በርክክብ…አሰራር ሊኖረው ይገባል።
	4. የባለአደራ ቦርድ የክፍያና የወጪ አጠቃቀም በስራ አመራር ቦርዱ እየታዩ እና እየተፈቀዱ ሊከፈል ይገባል።
	5. ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው ከተለወጡ ድርጅቶች የሚረከባቸው ሰነዶች የተሟላ ፣ኢኮኖሚያዊ ወይንም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እና የሌላቸውን ሰነዶች በመመሪያው መሰረት ተለይተው ሊረከብ ይገባል።
	6. ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ሰነዶችና ንብረቶች በኃላፊነት ሊይዝና ሊጠብቅ ይገባል።
	7. ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው የተቀየሩ የልማት ድርጅቶች ርክክብ እስከተፈጸመበት እለት ያለውን የሂሣብ ምዝገባና የሂሳብ መዝጋት ስራ እንዲከናወንና በውጪ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያደርግ ይገባል።
	8. ባለአደራ ቦርዱ ይዞታቸው ለተቀየሩ ልማት ድርጅቶች በተዘጋው ሂሳብ

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issue)	የኦዲት መስፈርት (Audit Criteria)
	መሰረት የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ሊያዘጋጅ ይገባል።
	9.ባለአደራ ቦርዱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመሰብሰብ እና ተከፋይ ሂሳቦችን ለመክፈል የሚያስችል ዕቅድ ሊያዘጋጅና በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል።
	10.በባለአደራ ቦርዱ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት ዓመታዊ መርሃ ግብር ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።
	11.ባለአደራ ቦርዱ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያዘጋጅ ይገባል።
	12. የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሳባቸውን አስታርቀው ለቦርዱ ማስተላለፍ ይገባቸዋል።
	13.በባለአደራ ቦርዱ ተጣርተው ከቀረቡት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በህግ እንዲጠየቁ ከመረጃ ጋር ወደ ህግ ክፍል ሊተላለፍ ይገባል።
	14.በባለአደራ ቦርዱ ከተረከባቸው ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች ጊዜ ያለፈባቸው እና ሊሰበሰቡ ወይንም ሊከፈሉ የማይችሉትን አጣርተው ከመዝገብ የመሰረዝ ለመንግስት ሃሳብ ሊያቀርቡ ይገባል።
	15. የሚከፈሉ ተከፋይ ሂሳቦች ከመከፈላቸው በፊት በአግባቡ ተጣርተው መቅረባቸውንና በሚመለከተው ኃላፊ መፅደቃቸው ሊረጋገጥ ይገባል።
	16.በህግ ወይንም በኪሳራ ምክንያት የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸው በወቅቱ ተዘግቶ ያላቸው ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል።
2.የባለአደራ ቦርድ ይዞታቸው ከተቀየሩ ወይንም በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ንብረቶች አያያዝ ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በመመሪያ መሰረት መሆኑን እንዲሁም የዋጋ ግመታው (valuation) ስርአት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን፣ ስኬታማና ቅልጥፍናን በጠበቀ መልኩ መተግበሩን ማረጋገጥ፣	17. የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅ ና አወጋገድ መመሪያ ሊኖርና በመመሪያው መሰረት ሊተገበር ይገባል።
2.1ባለአደራ ቦርዱ በኪሳራ ምክንያት የተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው የተቀየሩ የልማት ድርጅቶች ንብረት	18.ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶችን ለማስወገድ የሚያስችል ዕቅድ ሊያዘጋጅና በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል።

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issue)	የኦዲት መስፈርት (Audit Criteria)
አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እያከናወነ መሆኑን ማጣራት፣	19.በኪሳራ ምክንያት የሚፈርሱ ድርጅቶችን ንብረት ለማስወገድ ቦርዱ ለብቻው በፕሮጀክት መልክ ቀርጾ እቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡
	20.የሚፈረሱ የልማት ድርጅቶች በተናጠል ንብረቶችን ከመሸጥ በፊት በጠቅላላው ሊሸጥ እንደሚችል በቅድሚያ ሊታይ ይገባል፡፡
	21.ባለአደራ ቦርዱ የሚረከባቸውን የተለያዩ ንብረቶች በንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡
	22.ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች ለሽያጪ በሚያመች መልኩ(በሼልፍ፣በዓይነትና በኢንዴክስ) ማደራጀት ይኖርበታል፡፡
	23.ባለአደራ ቦርዱ የሚረከባቸው ቋሚና አላቂ ንብረት ፣ጥሬ ዕቃና ምርት በመዝገብ በሚታየው መጠን ለመሆኑ ዝርዝር የማስታረቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
	24.ባለአደራ ቦርዱ የተላለፉለትን ንብረቶችን ለመሸጥ የሚጠቀምበት የመሸጫ ዘዴ ጨረታ ወይም ሐራጅ ሊሆን ይገባል፡፡
	25.ባለአደራ ቦርዱ ለአክሲዮን ማህበራት የውክልና ንብረት ሽያጪ ለመስጠት የሚያስችሉ ቅድሚያ የተቀመጡ መስፈርቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡
	26.ባለአደራ ቦርዱ የውክልና ንብረት ሽያጪ ውል ከአክሲዮን ማህበራት ጋር ሲዋዋል ውክልናው(የጊዜ ገደብ ፣ሪፖርት አደራረግ ስርዓት ፣ኮሚሽን መጠን ወዘተ) የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡
	27.ለጨረታ የሚቀርቡ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ የይዞታ ማረጋገጫ(ለምሳሌ ካርታና ፕላን) እንዲሁም የማስወገድ ህጋዊ ስልጣን ያለ መሆኑ እየተረጋገጠ ለጨረታ ሊቀርቡ ይገባል፡፡
	28. ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች በአንድ ጊዜ በጥቅል መሸጥ አለበት፡፡
	29. ባለአደራ ቦርድ ንብረቶችን በታትኖ የመሸጥ አፈጻጸም መከተል ያለበት በውዳቂነት ማስወገድ ሲኖርበት ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡
	30. የጨረታ አሸናፊዎች በጨረታ በተገለፀው ቀነ ገደብ ውስጥ የሽያጭ ውል በመፈራረም፣ ያሸነፉበትን ዋጋ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (ሲ ፒ ኦ) በሙሉ አጠናቀው መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡
	31.የጨረታ አሸናፊዎች ያሸነፉበት ንብረት ርክክብ የሚፈፀመው የከፈሉት

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issue)	የኦዲት መስፈርት (Audit Criteria)
	ገንዘብ በሚመለከተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆን ይገባዋል።
	32.የጨረታ አሸናፊዎች ያሸነፉበትን የንብረት ዋጋ እንዲከፍሉ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው ክፍያውን ያላጠናቀቁ እንደሆነ ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ከጨረታው ሊሰረዙ ይገባል።
	33.ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል።
	34. ባለአደራ ቦርዱ ተረክቦ ለሚያስተዳድራቸው በመጋዘን ውስጥ ላሉ ንብረቶች የእሳት አደጋ መከላከያ፣ለጥንቃቄ የሚረዱ ጽሁፎች እና ተገቢው ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።
	35.የንብረት መዛግብቶች የመያዝ፣ የመረከብና ወጪ የማድረግ ኃላፊነት በአንድ ሠራተኛ ብቻ መሰራት የለበትም።
2.2.ባለአደራ ቦርዱ በኪሳራ ምክንያት ከተዘጉ እና በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተቀየሩ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸው ንብረቶች ዋጋ ግመታ (valuation) ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማጣራት፣	36.ንብረቶች በሽያጭ ከመወገዳቸው በፊት የመነሻ ዋጋው ከንብረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የመንግስት መሰሪያ ቤቶች እንዲያማክሩት ሊጠይቅ ይገባል።
	37.በንብረቶች የዋጋ ግመታ ወቅት ባላአደራ ቦርዱ ከባለሙያው ጋር በመሆን ንብረቱን በአካል በመገኘት ይዘቱን ማወቅ ፣ተመሳሳይ ዕቃ ከሚያቀርቡ አቅራቢዎች ላይ የወቅቱን የገበያ ዋጋ መረጃ መሰብሰብና የመነሻ ዋጋ መወሰን ይገባል።
	38.በተደጋጋሚ ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶች ከመነሻ ዋጋ በታች ምን ያህል ፐርሰንት ዝቅ ቢሉ ንብረቶችን መሸጥ እንደሚገባ ሊወሰን ይገባል።

አባሪ 2

ባለአደራ ቦርድ ከሚገለገልበት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተሟላ ሁኔታ የማይተገብራቸው አንቀጾች

- የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የንብረት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 9/2003 ባለአደራ ቦርዱ ሊከተላቸው የሚገቡ ነገር ግን የማይተገበሩ አንቀፆች ውስጥ አንቀፅ 20 የሚወገዱ ንብረቶች የነጠላ ዋጋቸው ከ1,000 በላይ ከሆነ እና በአንድ ጊዜ ለሽያጭ የሚቀርቡ ከ100,000 በላይ ከሆነ የሚያስወግደው የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ነው፤ እንዲሁም ከብር 1,000 በላይ የሆኑ የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር መረጃ በየጊዜው ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል ቢልም ማይቀርብ መሆኑ፣
- አንቀፅ 22 የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ "እንዲሸጡ ውሳኔ የተሰጠባቸው የመንግስት ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ ያወጣል…" ቢልም በባለአደራ ቦርድ አሰራር መሰረት የጨረታ መነሻ ዋጋ በዋጋ ገማች ኮሚቴ የሚሰራ መሆኑ፣
- አንቀፅ 23 እንዲወገድ የተወሰነበት እያንዳንዱ የመንግስት ንብረት የወቅቱን መነሻ ዋጋ ንብረቱን በሚያስተዳድረው ክፍል ይገመታል ይላል ነገር ግን የዋጋ ግመታው ንብረቱን በሚያስተዳድረው ክፍል ሳይሆን አስወጋጅ ኮሚቴ የጨረታ መነሻ ዋጋ የሚገምት መሆኑ፤ ህንፃና ተመሳሳይ ግንባታዎች የባለቤትነት መብት የተሰጠው ለፌዴራል መንግስት በመሆኑ እነዚህን ንብረቶች ለማስወገድ ቢፈለግ ሚኒስቴሩን ማስፈቀድ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል። ነገር ግን ሁሉንም አይነት ንብረት ካለምንም ፈቃድ የሚያስወግድ መሆኑ፣
- አንቀፅ 24 ንብረቶች ለሕዝብ በሐራጅ ወይንም በጨረታ ከመሸጥ በፊት የመንግስት መ/ቤቶች ለማስወገድ የፈለጉትን ንብረት በቅድሚያ ወደሌሎች መ/ቤቶች ለማዛወር መሞከር ይገባል። ዝውውሩም በወቅቱ የንብረት ዋጋ ግምት መሆን እንዳለበት ተቀምጧል። ነገር ግን ባለአደራ ቦርድ የመንግስት መ/ቤቶችን እንደማይጠይቅ እንዲሁም ድርጅቶቹን ለገዙ ፋብሪካዎች መለዋወጫ ሲጠየቁ በመዝገብ ዋጋቸው እንደሚፈቀድላቸው፣
- አንቀፅ 25 የተሸጡ ንብረቶች ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ እንዳለበት ቢጠቀስም መ/ቤቱ የሽያጭ ገንዘቡን ወደ ልዩ ፈንዱ ገቢ የሚያደርግ መሆኑ ፣

አባሪ 3

ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች በውክልና የሚሸጡ አክሲዮን ማህበራት ዝርዝር

1. በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር
2. አዲስ መካኒካል / አዲስ መለዋወጫ አ/ማ /
3. ወይራ ትራንስፖርት አ/ማ
4. ኮሜት ትራንስፖርት አ/ማ
5. ባቱ ኮንስትራክሽን አ/ማ
6. አዋሽ ኮንስትራክሽን አ/ማ
7. እርሻ መሳሪያዎች አ/ማ
8. ህንጻ ዲዛይን አ/ማ
9. ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን አ/ማ
10. ኢትፍሩት አ/ማ
11. ኢፋርም አ/ማ
12. ፋርሚድ አ/ማ
13. የህዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ንብረት
14. የብሄራዊ ትምባሆ ሞኖፖል /በኢትዮጵያ/
15. የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖራሽን ንብረት